**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

**ኖርዌይ ክፍል** Norway Section Norge avd.

**ዘገባ**

31.08.2009

## የትውልድ ትውስታ በኢሕአፓ 37ኛው የምስረታ ዓመት በዓል ላይ፣

የኢሕአፓ ምስረታ 37ኛው ዓመት በዓል በኖርዌይ-ኦስሎ ቅዳሜ ኦገስት 29 ቀን 2009 በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ዋለ።

በዚሁ በርካታ የድርጅቱ አባላት፣ ደጋፊዎችና ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት በተከበረው በዓል ላይ በጓድ አሊ ሰኢድ በሕይወትና በትግል ጓዶቹ ዙሪያ የሚያጠነጥነው "የትውልድ ትውስታ" የተሰኘው ፊልም ለታዳሚው ቀርቧል በዕለቱ ለዛ ባለው የእንካስላንትያ ወጋ፣ ግጥም፣ መነባንብና ቅኔ እያዋዛ እየመከረና እያስተማረ ተሰብሳቢውን ያስደመመው ባለታሪክ ጓድም በቦታው የነበረ ሲሆን፣ ፊልሙ ትውልዱ ካለፈበት ሰፊ የትግል ውጣ ውረዶች አንዷቷን ፀጉር የመምዘዝ ያህል ነው በማለት ሲሆን አያያዞም የፊልሙ ዕሴት ቂም ከመቋጠር ይልቅ የነበረውን ሁኔታ የሚያሳውቅ ማኅደርን ለተተኪው ትውልድ ማቆየትና ለቀጣይ የተሻለ እርምጃ ፈርን ለመቅደድ መሆኑን ገልጿል።

የበርካታ ሰዎችን ስሜት የያዘውና አዳራሹን በዝምታ ድባብ ገዝቶት በነበረው በዚህ ፊልም ላይ በኖርዌይ የወጣት ሮድ ፓርቲ (Partiet Rødt) ተወካይ ወት ሲሀር አይዳር (Siher Aydar) ፊልሙ በኢትዮጵያ ስለነበረውና አሁን ስላለው ሁኔታ ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን እንዳስጨበጣትና በቀጣይ ከወጣት ማኅበራት ከትምህርት ቤቶችና ከፓርቲዋ አካላት ጋር ለውይይት እንደምታቀርበው የጠቆመች ሲሆን ለመጨረውም ከፓርቲው እንቅስቃሴ ጋር በጋራ ለመሥራት ማቀዷን ጠቁማለች።

በዚሁ ዕለት ከተመሰረተ ጥቂት ጊዜያትን ያስቆጠረው ነገር ግን በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ያለው የኢሕአፓ ወክንድ ተወካይ ንግግር ያደረገ ሲሆን ለኖርዌይ ወጣቶች በጠነከረ መሰረትና መስዋዕትነት የተጀመረውን የኢሕአፓን ዓላማ በመረከብ እጅ ለእጅ ተያይዘን መዝለቅ እንዳለብንም ከአደራ ጭምር አሳስቧል።

በተጨማሪም የድርጅቱን ምስረታ በዓልን አስመልክቶ ከኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ የተላከው ቀስቅሽና አበረታች መልዕክት በአቶ ጌትነት ውብሸት የተነበበ ሲሆን፣ ለፊልሙ አዘጋጅና ለወክንዱ ተወካይ በኖርዌይ አክሽን ኮሚቴና በኖርዌይ የወጣት ክንፍ አማካኝነት የምስጋናና የመታሰቢያ ስጦታዎች ተበርክቶላቸዋል።